Amharic

# የቆሻሻ ማስወገድ አገልግሎቶች መመሪያ




## የ GO ጊዜ ነው!

GOVERNMENT OF WESTERN AUSTRALIA

WasteSorted
A Waste Authority Program

City of Wanneroo




# አዲሶቹን የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በሰፈሩ ውስጥ ማስተዋወቅ

አዲሱ የሶስት አይነት ማጠራቀሚያ ስርዓታችን እያንዳንዱ ሰው ቆሻሻውን ወደ ትክክለኛው ቦታ እንዲያደርስ ይረዳል። ግራ መጋባቱን ለመቀነስ እና የአውስትራሊያ ደረጃዎችን ለማሟላት የማጠራቀሚያ ክዳናችንን ቀለም ቀይረናል። ማጠራቀሚያዎችን በትክክል በመጠቀም ውድ ሀብቶችን ወደ ቆሻሻ መጣያ እንዳይሄዱ እና አካባቢያችን ለመጪው ትውልድ እንዲጠበቅ ማድረግን እናግዛለን።

## የትኛው ማጠራቀሚያ ውስጥ እንደሚያስገቡ እርግጠኛ አይደሉም?
## የ Recycle Right መተግበሪያን ያውርዱ!

የRecycle Right መተግበሪያ ነገሮችን በየትኛው ማስቀመጫ ውስጥ እንደሚያስገቡ ለማወቅ ቀላል እና ምቹ መንገድ ነው። የሚከተሉትን አካቷል:

- Which Bin - በየትኛው ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ምን አይነት ቆሻሻ እንደሚገባ እና እዚያ መግባት የሌለበት ምን እንደሆነ እና ትክክለኛውን የማስወገጃ ዘዴዎች በቀላሉ ይወቁ።
- ልዩ ልዩ ቆሻሻዎችን በትክክል እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ የሚነግርዎት ከ A እስከ Z ዝርዝር።
- Find My Nearest - እንደ ባትሪ ድንጋዮች፣ የመኪና አካሎች፣ የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻዎች እና ሌሎችንም ፕርዝ ከተማ አካባቢ በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከል ወይም ቆሻሻ መጣያ ቦታ ለማወቅ እና አቅጣጫዎችን ለማግኘት ያስችልዎታል።




App Store ለ iOS ተጠቃሚዎች

Google Play Store ለ Android ተጠቃሚዎች

recycle right

recycleright.wa.gov.au

# በየሰፈሩ፣ ወደ አጠቃላይ የቆሻሻ ማጠራቀሚያቸው በ 60% ያነሰ ቆሻሻ የሚከቱ ታላላቅ ሰዎች አሉ ።




## ታዲያስ ፣ እኔ ’ጂ’ ነኝ!

እኔ ወደ ቆሻሻ መጣያ መሄድ ለማይገባቸው በጣም ጥሩ ለሆኑ ነገሮች አዳዲስ ሚና መፈለግ ላይ ትኩረት አደርጋለሁ። ለበጎ አድራጎት ሱቆች፣ ለጓደኞቼ እና ለጎረቤቶቼ እቃዎችን እሰጣለሁ ። ነገሮችን ኢንተርኔት ላይ እሸጣለሁ እናም እኔ የአካባቢያችን ‘ምንም አትግዛ’ (Buy Nothing) ማህበራዊ ሚዲያ ቡድን አባል ነኝ።




## ጤና ይስጥልኝ፣ ‘አር’ ነኝ!

እኔ የገባኝ ሰው ነኝ። እነዚህን 5 የእቃ አይነቶች፣ ማለትም ቆርቆሮዎች፣ ወረቀቶች፣ ካርቶን፣ ብርጭቆ እና ፕላስቲክ ጠርሙሶች እና ጀሪካኖች ባለ ቢጫ ክዳን መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያ ውስጥ ብቻ እንደምናስገባ አውቃለሁ። ካርቶን የተጠፈጠፈ መሆኑን አረጋግጣለሁ እንዲሁም ጀሪካኖችቼን ካለቀለኩ በኋላ ክዳኖቻቸውን አስቀራለሁ።




## ታዲያስ ፣ እኔ ’ኢ’ ነኝ!

የምግብ ትርፍራፊዎች እና የአትክልት ቦታ ቆሻሻዎች ወደ መሬት በመመለስ ጥሩ ብስባሽ ሊሆኑ እንደሚችሉ አውቃለሁ። እኔ ለአትክልት ስፍራችን ማዳበሪያ እንዲሆን በቤት ውስጥ የብስባሽ ማጠራቀሚያ አለኝ እና በ ShareWaste አማካኝነት ጎረቤቶቻችን ለምግብ ትርፍራፊዎቻቸው ሁለተኛ የማገልገል ዕድል እንዲሰጡ እረዳቸዋለሁ።




## ጤና ይስጥልኝ፣ እኔ ’ኤ’ ነኝ!

ቆሻሻዎን ለመቀነስ በጣም ጥሩው መንገድ በመጀመሪያ ደረጃ ቆሻሻው እንዳይኖር ማድረግ ወይም ማስወገድ ነው! የሚጣሉ ኩባያዎችን፣ አላስፈላጊ የፕላስቲክ መጠቅለያዎችን እና ከረጢቶችን አልፈልግም እላለሁ! እኛ ከሚያስፈልገን በላይ ብዙ ምግብ ላለመግዛትም እንዲሁ የግዢ ዝርዝሬ ላይ የጭረት ምልክት አደርጋለሁ።




## ታዲያስ፣ እኔ ’ቲ’ ነኝ!

ብክነት በቤት ውስጥ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ስለሚገባው ነገር ብቻ አይደለም። ችግር ያለባቸውን ዕቃዎች በሳጥን ውስጥ አድርጌ ወደ ልዩ የመውደጃ ቦታ መውሰድ እንዳለብኝ ሁልጊዜ አስታውሳለሁ።

## ታላቅ ሰው ይሁኑ!

ቆሻሻ መሬት ውስጥ መቅበር የመጨረሻው አማራጭ ነው።




# እንደገና ጥቅም ላይ ለሚውሉ ማጠራቀሚያ




ፕላስቲክ

## የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና መያዣዎች


የምርት መያዣ ቅርጫቶች


የእርጎ መያዣ እቃዎች


የማጣፈጫ (ሶሥ) ጠርሙሶች


የአይስክሬም መያዣዎች


የመጠጥ ጠርሙሶች


የይዘው ይሂዱ መያዣዎች


የመታጠቢያ ክፍል ሳሙና ጠርሙሶች


የልብስ ማጠቢያ ሳሙና ጠርሙሶች



በፐርዝ ውስጥ የጀሪካን ክዳኖችን አውልቀን በአጠቃላይ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እናደርጋቸዋለን።






# የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ




ፕላስቲክ

## ለስላሳ ወይም ‘የሚጨፈለቁ’ ፕላስቲኮች



የፕላስቲክ ፓኬቶች



ጆንያዎች እና የማደበሪያ ከረጢቶች



የፕላስቲክ ከረጢቶች



ብዙ ሰዎች ለስላሳ ፕላስቲኮችን በአካባቢው ወዳለው መደብር እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይወስዳሉ።

ለበለጠ መረጃ redcycle.net.au ን ይመልከቱ

## ሌሎች የቤት ውስጥ ፕላስቲኮች



የኛ ሰፈር ፖሊስቲሪንን (ትላስቲክ-ነክ እቃዎች) እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ወደ ቆሻሻ ማዕከል በመውሰድ በቆሻሻው ማጠራቀሚያ ውስጥ ቦታን ይቆጥባል።



ፖሊስቲሪን



አጠቃላይ የቤት ፕላስቲክ ዕቃዎች



የሚጣሉ የሚወሰዱ ምግቦች (ቴክአወይ) ዕቃዎች



ብዙ ሰዎች የሚጣሉ እና የነጠላ-ጥቅም ዕቃዎችን በዘላቂ እና እንደገና ጥቅም ላይ በሚውሉ አማራጮች እየተኩ ነው።

# ወረቀት እና ካርቶን

## እንደገና ጥቅም ላይ ለሚውሉ ማጠራቀሚያ



የእንቁላል ካርቶኖች



ከካርቶን የተሰሩ ቱቦዎች



ሳጥኖች



የጽሑፍ ወረቀት



ከካርቶን ወረቀት የተሰሩ የፈሳሽ መያዣዎች



ፖስታዎች




ጋዜጦች እና መጽሔቶች




የተዘረጋ ካርቶን ቦታን ይቆጥባል እንዲሁም ነገሮች እንዳይቀረቀሩ ያደርጋቸዋል።

## የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ



በፎይል (ብልጭልጭ ወረቀት) የተለበጡ ካርቶኖች



የይዘው ይሂዱ ኩባያዎች



የተቀዳደደ ወረቀት




የቆሸሸ ወረቀት እና ማሸጊያ ካርቶን



ቲሹዎች እና የወረቀት ፎጣ




በቤት ውስጥ ላለው ማዳበሪያ ማጠራቀሚያ እንዲሆን የተቀዳደደ ወረቀት እና የወረቀት ፎጣዎች እሰበስባለሁ።




# እንደገና ጥቅም ላይ ለሚውሉ ማጠራቀሚያ



ቆርቆሮዎችና ጣሳዎች



የብረት ክዳኖች



ወደ 5 ሴ.ሜ ዲያሜትር ኳስ የተጠቀለለ የአሉሚኒየም ፎይል (ብልጭልጭ ወረቀት)




10 ሳንቲም ተመላሽ ለማድረግ ብቁ የሆኑ ባዶ የመጠጥ ኮንቴይነሮችን ወደ አካባቢያችን ተመላሽ ማድረጊያ ማዕከል እንወስዳለን። ተጨማሪውን ገንዘብ ለትምህርት ቤቶች፣ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ለክለቦች እናጋራለን።




# የቆሻሻ መጣያ ማዕከል

wanneroo.wa.gov.au/recycleright

## አደገኛ ይዘቶች ያላቸው ጣሳዎች



ብናኝ የሚረጩ ጣሳዎች




ቀለም

ለሌሎች አደገኛ ቆሻሻ ዓይነቶች ገጽ 13 ን ይመልከቱ

ብረት




# እንደገና ጥቅም ላይ ለሚውሉ ማጠራቀሚያ






ጠርሙሶች እና ጀሪካኖች





የመጠጥ ብርጭቆዎች



የሚጣሉ ዕቃዎች ከምግብ ቅሪት ነፃ እንዲሆኑ በማጠብ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ከፍ እናደርጋለን።




## የቆሻሻ መጣያ ማዕከል

wanneroo.wa.gov.au/recycleright

## ሌሎች የቤት ውስጥ ብርጭቆዎች



የዓሳ ገንዳዎች



ዕቃዎችን በስጦታ ለመስጠት እና የአንድ ሰው ቀን ብሩህ ለማድረግ ብዙ መንገዶች አሉ። ዕቃዎችን ማድረስ፣ ለጎረቤቶች በስጦታ መልክ መስጠት፣ መለዋወጥ ወይም መሸጥ ይችላሉ።



መስተዋቶች



የመስታወት ጠረጴዛዎች




# የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ



## የተክል እና የእንስሳት ተዋጽኦ ምግብ



ስጋ



የወተት ተዋጽኦ



የፍራፍሬ እና የአትክልት ልታጮች



ሩዝ እና ጥራጥሬዎች



ብዙ ሰዎች በቤታቸው የምግብ ትራፊዎችን ወደ መሬት የመመለስ ሥራ ይሰራሉ። ብዙ መንገዶች አሉ - የትል እርሻ ፣ የብስባሽ ማጠራቀሚያዎች፣ ዶሮዎች፣ ቦካሺ ወይም ብስባሽ ለሚያዘጋጅ ጎረቤት መስጠት። ወደ ቆሻሻ መጣያ ቦታ የምግብ ትራፊዎችን ከመላክ መቆጠብ ቀላል ነው ። ለዋነሮ ከተማ ነዋሪዎች የዘጋጁ ሽልማቶችን switchyourthinking.com.au ላይ ያግኙ




# የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ





የአፍ ጤና አጠባበቅ



ተጣባቂ ባንዴጆች



ናፒዎች እና የሚጣሉ የንፅህና መጠበቂያ ዕቃዎች




# የአትክልት ቦታ የተክል ቆሻሻ (GO) ማጠራቀሚያ



ትናንሽ ቅርንጫፎች

*ከፍተኛው 100 ሴ.ሜ ርዝመት*

*ከፍተኛው 6 ሴ.ሜ ስፋት*




ትላልቅ የክርክም ቁርጥራጮችን ለዓመታዊው የጅምላ አረንጓዴ የመንገድ ዳር መሰብሰብ ያቆዩ። ንጹህ አረንጓዴዎችን ወደ ታዋቂው ዋንጋራ ግሪንስ ሪሳይክል ፋሲሊቲ ፣ 70 Motivation Drive, Wangara. ለመውሰድ ቫውቸራችንን እንጠቀማለን።



በእርስዎ የ ‹GO› መያዣ ውስጥ ምንም የፕላስቲክ ከረጢቶች አይገቡም



ቅጠሎች



ቀንበጦች እና ጭራሮዎች



የአትክልት ቦታ ክርክም ውዳቂዎች



የሣር ቁርጥራጮች እና አረም

የ ‹GO› ቢን የለዎትም? የአትክልት ቦታ የተክል ቆሻሻዎችን በአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎ ውስጥ ያስገቡ።




የአትክልት ቦታ የተክል ቆሻሻ

ሌሎች የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች




# የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ





የአልጋ ልብስ እና ሊኖ




በዋነሩ ከተማ ውስጥ የቤት ውስጥ እቃዎችን እንሰጣለን፣ እንለዋወጥ እና እንሸጣለን። የሌላውን ሰው ቀን ብሩህ ያደርገዋል ወደ ቆሻሻ መጣያ ሄዶ መቀበርንም ያስቀራል።



የቆዩ አልባሳት እና ጨርቃ ጨርቆች



# ዓመታዊ ደረቅ የጅምላ ቆሻሻዎችን መሰብሰብ

የከተማው መስተዳደር ዓመታዊ የመንገድ ዳር ላይ የጅምላ ቆሻሻ ክምችት መሰብሰብ አገልግሎት ይሰጣል። ቆሻሻ ከታቀደው መሰብሰብ ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በመንገድ ዳር ላይ መቀመጥ አለበት። እባክዎ wanneroo.wa.gov.au/bulkwaste. በመጎብኘት ቆሻሻ የመሰብሰብ ቀንዎን ያረጋግጡ። ቆሻሻ የመሰብሰብ ሠራተኞች እድሉ አንዴ ካመለጠት፣ ተመልሰው አይመጡም።



ፍራሽዎች



የቤት ዕቃዎች



ግዙፍ የቤት ውስጥ ቆሻሻ



ነጫጭ እቃዎች (ፍርጅን የመሰሉ)

ቁሳቁሶችን ለመሰብሰብ ለማሽኖች የሚሆን ቦታን በመተው ቆሻሻውን በጠርዙ ላይ በጥሩ ሁኔታ ያስቀምጡ።

# የቆሻሻ መሰብሰብ መስፈርቶች

## ማጠራቀምያችዎን እንዲሰበሰቡ ማቅረብ

6am

በእርስዎ የመሰብሰብያ ቀን እስከ ጠዋት 6 ሰዓት ድረስ ማጠራቀምያዎችን ውጪ ያስቀምጡ

70 kg

የእያንዳንዱ ማጠራቀምያ ክብደት 70 ኪ.ግ ነው

በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ፊት ለፊት መኪና አያቁሙ እና መንገዶችንም ግልጽ ያድርጉ

ከተሰበሰበ በኋላ ማጠራቀምያዎን በግቢዎ ወሰን ውስጥ ወዳለው ማስቀመጫ ቦታ በተቻለ ፍጥነት ይመልሱ






ከዛፎች ቢያንስ 1 ሜትር ያርቋት እና ከዛፍ ጥላ ስር አይሁን

በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች መካከል ቢያንስ 1 ሜትር ክፍተት ያድርጉ

ከመኪናዎች፣ ከፖስታ ሳጥኖች እና ከአጥር ወዘተ ቢያንስ 1 ሜትር ያርቁ

## የጅምላ ቆሻሻዎ እንዲሰበሰብ ማቅረብ





ቁሳቁሶችን ለመሰብሰብ ለማሽኖች የሚሆን ቦታን በመተው ቆሻሻውን በጠርዙ ላይ በጥሩ ሁኔታ ያስቀምጡ።

- የእግረኛ መንገዶችን፣ ጠባብ መንገዶችን እና የመኪኖችን ከግቢ መውጫ-መግቢያ መንገዶችን ግልፅ ያድርጉ። ቤትዎ በጠባብ መንገድ ዳር ላይ የሚገኝ ከሆነ፣ እባክዎን በቤትዎ ፊት ለፊት ባለው የእንግዶች የመኪና ማቆሚያ በአንዱ ውስጥ የጅምላ ቆሻሻውን ያኑሩ።
- ጉዳት እንዳይደርሱ ለማድረግ እባክዎን ቆሻሻውን ከአጥሮች፣ ግድግዳዎች፣ ዛፎች፣ የፖስታ ሳጥኖች፣ የህዝብ መገልገያዎች፣ የኃይል ጉልላቶች ፣ የውሃ ቆጣሪዎች እና የውሃ መርጫዎች ቢያንስ 1 ሜትር ርቀት ላይ ያኑሩ።
- እቃዎችን ቀለም በተቀቡ የመንገድ ዳሮች እና ሰው ሰራሽ ሣር ላይ አያስቀምጡ። ተሽከርካሪዎች ምልክቶችን ብልሽትም ሆነ ጉዳት እንዳይፈጥሩ በእነዚህ ቦታዎች ላይ የተቀመጡ ነገሮችን መሰብሰብ አንችልም።
- ቆሻሻዎን ለመሰብሰብ የት እንደሚቀመጡ እርግጠኛ ካልሆኑ የከተማውን መስተዳደር በ 9405 5000 ያነጋግሩ።

# አከባቢን ማቆሸሽ እና ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ቆሻሻን መጣል

በዋነሩ ከተማ ውስጥ የምንኖርበትን መሬት እንወዳለን። ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ቆሻሻን መጣልን ሪፖርት በማድረግ ንፅህናውን እንዲጠበቅ ሊረዱ ይችላሉ

- የከተማዋን ጠባቂዎች በ **9405 5000** ወይም **1300 138 393** ከሥራ ሰዓት በኋላ
- የውሃ እና የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ ህገ-ወጥ የቆሻሻ መጣል የጥቆማ ስልክ መስመር **1300 784 782**
- የ ቆንጆዋ አውስትራሊያ አከባቢን የሚያቆሽሹትን ለመጠቆም (ከተሽከርካሪ ላይ ቆሻሻ ሲጣል ለመጠቆም) **kabc.wa.gov.au/report-littering**

በአከባቢዎ አንድ ቦታ እንዲፀዳ ማገዝ ይፈልጋሉ? ብዙ ነዋሪዎች ጊዜያቸውን ለ 'Adopt- a-Spot' ለመስጠት ፈቃደኛ ይሆናሉ። ዛሬ ይመዝገቡ በ **wanneroo.wa.gov.au/adopt-a-spot**


City of Wanneroo

23 Dundebar Road, Wanneroo, WA 6065

Locked Bag 1, Wanneroo, WA 6946

ቴ (08) 9405 5000
ከሥራ ሰዓታት በኋላ 1300 13 83 93
ኢ. enquiries@wanneroo.wa.gov.au
wanneroo.wa.gov.au


ይህ ሰነድ ወደ በርካታ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ለበለጠ መረጃ እባክዎን wanneroo.wa.gov.au/talkingmylanguage ን ይጎብኙ


processgreen™
environmentally sustainable printing

አረንጓዴ ኤሌክትሪክን በመጠቀም እና ከፍተኛ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ታትሟል።


በባለ ቢጫ ክዳን እንደገና ጥቅም ላይ በሚውል ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎ ውስጥ ይክተቱጡኝ።

# ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ




## እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያ

- ✓ የአሉሚኒየም እና የብረት ጣሳዎች
- ✓ የመስታወት ጠርሙሶች እና ገንቦዎች
- ✓ የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና መያዣዎች
- ✓ ንጹህ ካርቶን (የተዘረጋ)
- ✓ ወረቀት (ያልተቀዳደደ)




## የአትክልት ቦታ የተክል ቆሻሻ (GO) ማጠራቀሚያ

- ✓ የሣር ቁርጥራጮች
- ✓ ቅጠሎች/አበቦች
- ✓ የክርክም ውዳቂዎች እና ትናንሽ ቅርንጫፎች
- ✓ አረሞች፣ ጭራሮዎች እና ቀንበጦች




## የአጠቃላይ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ

- ✓ የምግብ ቆሻሻ
- ✓ የማይፈለግ ልብስ
- ✓ ናፒዎች/የንፅህና መጠበቂያ ዕቃዎች
- ✓ የተቆራረጠ/የቆሸሸ ወረቀት
- ✓ ቆሻሻ ካርቶን (የተዘረጋ)
- ✓ የእንስሳት እበቶች እና የቤት እንስሳት አይነምድር





### የማይፈለጉ መንገድ ዳር የሚከማቹ ደረቅ የጅምላ ቆሻሻዎች

ፍራሾች (የአልጋ)

ምድጃዎች እና ሌሎች ፍሪጅን የመሰሉ ነጫጭ እቃዎች (እስከ 1.5 ሜትር ርዝመት ያላቸው)

የቤት ዕቃዎች እና ሌሎች ግዙፍ የቤት ቁሳቁሶች

የተቆራረጠ ብረት



### መንገድ ዳር የሚከማቹ አረንጓዴ የጅምላ ቆሻሻዎች

ልቅ የዛፍ እና የቁጥቋጦ ክርክም ውዳቂዎች (እስከ 1.5 ሜትር ርዝመት እና 300 ሚሜ ዳያሜትር)



### በአከባቢው አስተዳደር ቁጥጥር የሚደረግባቸው የቆሻሻ መጣያ ማዕከላት

**Wangara Greens Recycling Facility** (ቅዳሜና እሁድ እና በህዝባዊ በዓላት ቀን ክፍት ነው)
70 Motivation Drive, Wangara
ስልክ: 9405 5000

**Tamala Park**
1700 Marmion Avenue, Mindarie
ስልክ: 9306 6303

**Recycling Centre Balcatta**
238 Balcatta Road, Balcatta
ስልክ: 9205 8555



ብዙ ሰዎች የሚከተሉትን ዕቃዎች ወደ ቆሻሻ መጣያ ማዕከል ይወስዳሉ። በእያንዳንዱ ማእከል ተቀባይነት ያለው ምን እንደሆነ ይህን ድረገፅ በመጎብኘት ያረጋግጡ **wanneroo.wa.gov.au/recycleright**

- ብናኞች
- ቀለም
- የመብራት አምፖሎች
- ኬሚካሎች
- የጋዝ ጠርሙሶች
- የእሳት ማጥፊያዎች
- መድሃኒቶች
- ባትሪዎች
- የሞተር ዘይት
- ጎማዎች
- ሞባይል ስልኮች
- የኤሌክትሮኒክ ቆሻሻ (ኢ-ቆሻሻ)
- የግንባታ ቆሻሻ
- አስቤስቶስ